# የፅናት ናሙና

በኤርሚያስ መኮንን

2000 ዓ.ም

# ምዕራፍ አንድ

"ዋ... ይ... ዋ... ይ... አም...እም... ወየው" የሚል የጣር ድምፅ በታፈነው አፏ እያሰማች የሰቆቃ ፊት አሳየች። ምራቁን ውጦ በላብ የራሰውን ፊቱን እያበሰ አንገቱን ቀልበስ አድርጎ አይኖቹን እያጉረጠረጠ "ዝም በይ አንቺ... ዝምበይ... ወዮልሽ... ከእንግዲህ አንዲት ቃል ትንፍሽ ብትይ አሳርሽን ነው የምትበይው" በማለት ግፍ መፈፀሙ አንሶት በጥፊ ሲመታት ከግድግዳው ጋር ተላተመች። የግድግዳው ግጭት ቢሰማትም ያለየሌለ ሀየሏን ተጠቅማ ኡኡ... ወይኔ እናቴ" እያሰች የሲቃ ድምፅ አሰማች።

የተሰማው የሰቆቃ ጩኸት ከመክበብ ጆሮ እንደገባ የትሪስት ድምጽ እንደሆነ ለመለየት ጊዜ አልወሰደበትም፤ ምን እንደሆነች ለማጣራት በፍጥነት ወደውስጥ ለመግባት በሩን ለመክፈት ቢሞክር አስወትሮው ከውስጥ ተቸንክሯል። በመታጠቢያ ቤቱ በኩል ባሰው መስኮት ዘሎ ባሰው ሰውነቱ እንደምንም ተንጠራርቶ አሾልቆ ሲመለከት ትርሲት ጥቅልል ብላ አንገቷን በእግሮችዋ መሀል ደፍታ ትንሰቀሰቃለች።

የተፈጠረውን ሀፍቱ ሰማወቅና ትርሲትን ለመጠየቅ በመቻከል የተቆለፈውን በር ማመን አቅቶት እንደገና ለመክፈት ቢታገልና ቢያንኳኳም ለግዜው ምንም መፍትሄ አላገኘም፤ እንደገና ወደ መስኮቱ ተመልሶ ሲመለከት

ትርሲት መንሰቅሰቋን ተያይዛዋለች። ፋታ አጣ። ድምፁን ጎላ አድርጎ "ትርሲት... ትርሲት... አረ ትርሲት... ደህና ነሽ... ሰምንድነው የምታለቅሽው... ምን ሆነሻል?" ሲል ገብረብሩክ ጣደፍ... ጣደፍ... ብሎ በሩን በኃይል በመበርገድ "ምንድነው እንዲህ የሚያስጮህህ?... ሰውን ከእንቅልፍ የምትነሳው?" በማለት የነገሩን ሥርመሰረት መክብብ አውቆ እንደሆነ ለማወቅ ፊቱን አነበበው። "ምንም" አይደለም ጋሼ ትርሲትን በመስኮት በኩል ስታለቅስ ስላየኋት ምን እንደሆነች ልጠይቃት ፈልጌ በሩ ከውስጥ ስለተዘጋብኝ ነው"።

ገብረብሩክ ትርሲት ሰምን እንዳለቀሰች መክብብን ሊያሳምኑ የሚችሉ ቃላቶችን ሲያውጠነጥን ቆየና ወደ ትርሲት ጋር በመሄድ ስሚ "አንቺ ዝም አትይም!" አለ ገብረብሩክ እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ።

ትርሲት የማትረባ ለስጋው ያደረ ሴሰኛ በማለት የስድብ ናዳ ስታወርድበት

"አንቺ ልክስክስ፡ ማንን ነው እንዲህ ብለሽ የምትሳደቢው ... እኔኑ ነው!" ብሎ አንድ ሁለቴ በጥፊ ሲላት ለቅሶዋን በእጥፍ ጨመረው። "ዋይ ...ዋይ ...እም ...እም ...ዋይ ...ዋይ ...ዋይ" ብላ እምባዋን አፍስሳ በእጆቿ ስትጠርገው እርጥበቱ ሲታይ ያለቀሰች ሳይሆን ውሃ የተደፋባት ይመስል ነበር።

የትርሲት ለቅሶ እረፍት የነሳው መክብብ የባሰ የሰቆቃ ድምጽ በመስማቱ እየፈራ እየቸረ አሁንም ሲያሾልት



እሷም ቀና ስትል አይን ለአይን ግጥምጥም ሲሉ "ትርሲት ...አንቺ ትርሲት ...ምን ሆነሽ ነው እንዲህ የምታለቅሽው " በለሆሳስ ሲላት ትርሲት ከማልቀስ በስተቀር መልስ አልነበራትም። "ንገሪኝ እንጂ" አለ ከአንደበቷ አንዲት ቃል እየጠበቀ። "ተ..ተ..ተ.ተወኝ ባ..ባእ ..ክህን" ስትል እሮሮ የተቀየጠበት ቃል ተናገረች።

"ምን ...ምን አልሽኝ? ትርሲት" ሲል እና ትርሲትም ተወኝ እባክህ ስትል በገብረብሩክ ጆሮ አሰተጋባ። የመክብብን ሁኔታ ሰመመርመር ተንደርድሮ በሩን በመክፈት "ማነው ..ማነው እሱ" በማለት ግቢውን ዙሪያ ገባውን ሲያማትር፤ "ፈለጉኝ እንዴ?" አለ መክብብ ለይምሰል መፅሃፍ ገልጦ የሚያነብ እየመሰለ።

ምን ያስጮህሃል ይልቁንስ ግቢውን ብታጸዳው ይሻልሃል።

አሁኑኑ አጸዳዋለሁ ጋሼ በማለት ትእዛዙን ለመፈጸም መንጎዳጎዱን ቀጠለ ገብረብሩክ ያሰወትሮው መታጠቢያ ቤቱን ለማጽዳት ይዋከባል። ጺሙን ተላጭቶ ውጎ ፊለስ አድርጎ የማያለቀልቀው ሰውዬ ለማስተካከል ተፍ ተፍ አብስቷል። ካጸዳዳ በኋላ የለበሰበውን የሹራብ እጂታ እየፈታ ወደ ሳሎኑ አቀናለሁ ሲል የትርሲት ታኮ ጫማ አደናቅፎት

ሊወድቅ፤ ‹‹እስይ እሰይ ገና ምን አይተህ አለች››መፍረጡ የአምላክ ኢምንት በቀል እንደሆነ እያመነች፡፡

ምን አልባት ያውጻቂ ልጅ ሳያውቅ አልቀረም እንዳወቀ ስማወቅ በጥያቄ ማጣደፉ የሚበጅ ይመስለኛል የነቃብኝ ከሆነስ ምን ይውጠኛ ይሆን ኧዎ ... አዎ አስወግደዋለሁ፤ አ! ....አ! ይሄማ አይደረግም፤ በራሴ ላይ መዘዝ ማምጣት ነው የሚሆነው፤ ይልቁንስ ሰበብ ደርድሬ እረጋሽን አሳምኜ በእሷ በኩል ደሞዝ ተስጥቶት እንዲባረር ይደረጋል፤ እያስ የተንኮል ሴራውን እያውጠነጠነ፤ ትርሲትን ካጎነበሰችበት ጸጉሯን ይዞ ቀና አደረገና "ምን የተለየ ነገር ደረሰብሽና ነው የሚያስነፈርቅሽ? የማንም ዱርዬ ከሚጫወትብሽ የሚታወቅና የተከበረ ሰው ሳይሻልሽ ቀርቶ ነው? ይልቁንስ ያባትሽ እጣ እንዳይደርስሽ፡ ያባትሽም ገንዘብ መና እንዳይቀር ላንድ ሰው ምንም ትንፍሽ እንዳትይ፡ አንቺ ውሃ ጠጪና ራሴን አሞኛል ብለሽ መኝታ ቤትሽ ግቢና ተኚ፡፡ ይህን ቃል ከጠበቅሽ እኔም ቃሌን ጠብቄ ጀርመን እህትሽ ጋር እንድትገናኝ አደርጋለሁ፡፡"

"አደራህን የበላህ፡ ቃልህን የጣስህ ቅሌታም፡ አንተ ብሎ ቃል ጠባቂ! 'የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንደሚባለው የስሞኑም ሁኔታ ለአንዳንተ አይነቱ ከሃዲ ተመቸው፡፡ ላንተ ቆሻሻ ስሜት ማርኪያ እኔን ሰው እንዳላምን፡ ሰው እንድጠላ



አድርገህ ተጫወትክብኝ፡፡ ብቻ እትዬ ይምጡ ጉድህን ነው የማፍረጠርጠው" ልትለው አስባ አንዳች ነገር ብቻ አንደበቷን ዘጋው፡፡ ውሃ ሊሰጣት እጁን የዘረጋውን ገፍትራ እንደምንም ብላ ከክፍሏ ገብታ ኩርምት አለች፤ ትራሱ ለመጨመቅ እስከሚችል በእንባዋ ጨቀየ፡፡ ገብረብሩክ የመጸዳጃ ክፍሉ በደንብ መጽዳቱን እየቃኘ በሃሳብ ተወጥሯል፡፡ "ይህ ውዳቂ ምናልባት አይቶኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ቆይ አንዳንድ ጥያቄ ላቅርብለትና ትንሽ አዝማሚያው ካላማረኝ ሁለተኛ እዚህ ስፈር ባይህ ድራሽህን ነው የማጠፋው ወይም ወህኒ ቤት ነው የማስወርድህ ብዬ አስፈራርቼ/ ደሞወዙን ስጥቼ/ ማባረር አለብኝ" አለና "አንተን እኮ ነው ስማኸኝ" ሲል "አቤት ጋሼ እኔን ነው?" ብሎ እየሮጠ እንደመጣ፡ "ና ወደዚህ" ብሎ ወደ በረንዳው ወስደውና ለመሆኑ "እኔ ለመጣ የት ነበርክ? እንዴት ለገባስ አላየኸኝም?"

"እኅር ምንጣፉን እያራገፍኩ ነበር"

‹‹በመስኮት ላይ ምን ነበር የሚያስጮህህ››

‹‹ሊንኪኒ ለምቼ ነው››

"ምን ጊዜ ነው ሲንኳኳ የለማኸው?"

"እርስዎ ከመታጠቢያ ቤት ወጥተው በሩን የከፈቱልኝ ጊዜ ከዚያ ትንሽ ቆየት ብሎ ነው"

"የቱ አካባቢ የተንኳኳ ይመስልሃል?" ትክክል የመለስ መስለውና የገብረብሩክን ከመታጠቢያ ቤት መውጣት አስታውሶ፡ የወዳደቀውን እቃ ሲያነሱ፡ ማለትም ትርሲት ያኮረፈቺው መታጠቢያ ቤቱን ስታጸዳ

መስታወት ሰብሬ ወይም እቃ ወድቆባት ጋሼ አጽድተው ሲወጡ ነው ብሎ አሰቦ "የተንጓጓው መታጠቢያ ቤቱ አካባቢ ይመስለኛል"

"ምን እንዳንጓጓው ታውቃለህ?"

ካሰበው ጋር በመገጣጠሙ እየገረመው፡ "እቃ ወድቆ ይሆን ብቻ እንጂ" ሲል ገብረብሩክ ብልጭ አለበትና "የተንጓጓው ምን እንደሆነ በደንብ እየታወቀህ ምን ሽፋንፋን------ ሽፋንፋን ታደርጋለህ? ትርሲት ተወኝ እባክህ ስትል ያልሰማኋት መሰለህ? ለመሆኑ ምን ብሰሃት ነው?

ስታለቅስ ኤይቻት ምን ሆነሽ ነው ሳላልኳት ነው፡፡

ምን ሆና እንደሆን የምታለቅሰው እያወቅህ ለምን እንደጠየካት ነው የገረመኝ እያለ ሲያውጣጣው ሲሞክር፤

እረ በእውነት ጋሼ ለምን እንዳለቀሰች እስከአሁንም አላወቅሁ በል ለማንኛውም ሌላ ጊዜ እንነጋገራለን፡፡ እሰውና ተመልሶ ልብሱን አወላልቆ ምንም አይነት የደም ምልክት እንዳይኖረው የቻለውን ያህል አጸዳድቶ ከቆሻሻ ልብስ ጋር አደባልቆ ሻወር ውስጥ ገብቶ ሲንቦጫረቅ ወ/ሮ አረጋሽ ገባች፡፡ እጋጣሚውን የማያውቅ እንግዳ ነገር እየገረማት "ገብረብሩክ ---- ኧረ ገብረብሩክ ዛሬ ምን ተፈጠረ? መኪናህን እውጭ ሳይ አለወትሮህ እኔን ቀድመህ መምጣትህ ሲገርመኝ፡ እኔን ሰውነትን መታጠብ በጥዋት ነው፡ ጥሩ ነቃ አድርጎ ያውላል እያልክ አንተ በማታው ገባህበት? ሚሽ ቶሎ ቶሎ በልና እርቦኛል እራት እንብላ" ብላ ጉድ ጉድ ማለት ያዘች፡፡



ወ/ሮ አረጋሽ መቸም የወጣላት ባለሙያ ነች፡፡ በአጭር ግዜ ውስጥ የምታበጋጃቸው ምግቦች ብዙ ስአታት የተደከመባቸው ነው የሚመስሉት፤ ተፍ ተፍ ብላ አቀረበችና መብላት እንደጀመሩ " ባይርበኝኖሮ ትርሲትን ጠብቀናት አብረን ብንበላ ጥሩ ነበር" ስትል ገብረብሩክ የሚያኝከውን እስኪውጥ አላስችል ብሎት "ተያት እባክሽ እሷ ትንሽ ጠገብ ብላለች"

"አይ ግፍ አትናገር ገብረብሩክ፡ እሷ ሌት ተቀን መጽሃፍ ከማንበብ በስተቀር ሰው ቀና ብላ የማታይ የአደራ ልጃችንን ጠገበች ትላለህ? ይቅር ይበልህ፡ በል እረፍና በላ" ስትለው "ተይ እባክሽ ብዙ የማታውቂው ነገር አለ፡፡ ከዚህ ሰፈር ዱርዬዎች ጋር የምታደርገው ሁኔታ ምኑም አላማረኝም፡፡ አንቺ ከመምጣትሽ በፊት ከጎረምሳ ጋር ስታወራ አይቻት ቆጣ ስላልኳት አኩርፋ ተኝታልሻለች" ሲላት

"ውይ አፈር በበላሁ፡ እቤት እያለች ነው ያልነገርከኝ? ደግሞስ ቁጣውን ምን አመጣው፡ አንተን በጣም ነው የምትፈራህ፡፡ ለምን አስደነገጥካት በኔ በሴቷ ያምር ነበር በዘዴ ለመቆጣቱም ለመምከሩም፤ ምን አስቸኮለህ ልጄ" ብላ ወደ ትርሲት መኝታ ቤት በመሄድ በሩን ከፍታ ወደ አልጋዋ በመጠጋት እንስላዋን ገለጥ አድርጋ የራስጌ መብራቱን ደመቅ እያደረገች

"ትርሲትዬ፡ ተነሽ የኔ ቆንጆ፡ እራትሽን ብዪ፡ አይዞሽ" ብላ ስትደባብሳት አይኗ በርበሬ መስሏል፡፡ ትራሷም በሽትጧል፡፡ " እንቅልፌ መጥቷል እልበላም" ብላ እንስላውን በግድ ተከናንባ ለጥ አለች፡፡

ገብረብሩክ ወ/ሮ አረጋሽን ተከትሎ ትርሲት ምን እንደምትል ለማዳመጥ በሩን ይዞ አንገቱን ወደ ውስጥ አስገብቶ ሲያዳምጥ፣ ወ/ሮ አረጋሽ እንደመከፋት እያለች "ምነው ----- ምን ብትናገራት ነው እንዲህ የሆነችው? በአግዜር በኩል ያስጠይቀናል። ሁለተኛ አንድ ነገር እንዳትናገራት" ኪዳኔ የውሸት ሳቅ ፈገግ ሲል ወ/ሮ አረጋሽ ቆጣ ብላ "ወልዴ ይሙት ሁለተኛ እንዳትናገራት" ብለው ወደ እራታቸው ተመለሱ።

ገብረብሩክ "እስቲ ዛሬ ጣሊያን ስታይል እንናድርገው" ብሎ የወይን ጠጅን ከመብላቱም በፊት አየበላም ገልብጦ ገልብጦ ሞቅ ብሎት ጠደፍ--- ጠደፍ ብሎ ሲጋደም ወ/ሮ አረጋሽ ሁኔታው ግርም ብሏት በቃ የኛ ህይወት እንዲህ ሆኖ ቀረ?እስ ጠዋት ማታ ስብሰባ የሚወጣበት የሚገባበት ስአት አይታወቅም

ወ/ሮ አረጋሽ በተራረፋቸው ላይ ሌላ እንጀራና ወጥ ጨማምራ ስጠታው እራቱን ቀማምሶ እንደወትሮው አየተፍለቀለቀ ደህና እደሩ እትዬ አላላትም። ወ/ሮ አረጋሽ ነገሩ ሁሉ ግራ ገባት። "ደሞ ይሄ ምን ሆነ? ቆይ ይብላና አጠይቀዋለሁ" ብላ ወደ ኪችን ስትመለስ ገብረብሩክ "በይ ደህና እደሪ ደከምኩልሽ" ብሎ አየተንገዳገደ ወደመኝታ ቤት ገብቶ ብዙም ሳይቆይ ግድግዳ የሚያንቀጠቅጥ ኩርፊያውን ቀጠለ።

"እ..እ..እ... ውይ ጋሼ ስለ እግዚአብሄር ልቀቁኝ፣ ወይኔ ወይኔ ..." የሚል ጩኸት ወ/ሮ አረጋሽ እንደሰማች ከትርሲት ክፍል እንደሆነ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀባትም።



ወዲያውኑ መብራት አብርታ ስታያት ትርሲት በቅዠት ትገለባበጣለች።

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ ምነው የኔ ልጅ" ብላ ስትደባብሳት እንደገና እንቅልፍ ሸለብ አደረጋት። ነገሩ በጣም ከነከናት። "መቆጣት ብቻ ሳይሆን ሳይደበድባት አይቀርም፣ ከቅዠቷ እንደምረዳው ስትለማመጠው እንደነበር ነው። ይህን ያህል ጭካኔ ከየት አመጣው" እያለች በመገረም ስለ ገብረብሩክ የዋህነት፣ እንዴት እንደሚያከብራት፣ እንዴት የሚያስቃት ብቻ ለሷ የሆነላትን ስለሱ ጥሩ ጥሩ ነገሩን ብቻ እያሰበች "ወቸ ጉድ ዛሬ ምን ነካው ይባላል፣ የሚደንቅ እኮ ነው" ስትል

መክብብ የበላበትን ሲያጣጥብ የወ/ሮ አረጋሽን ድምጽ በመጠኑ በመስማቱ "እመት እትዬ አናገሩኝ?" አለ

"ውይ መክብብ ሰማኸኝ እንዴ? በረንዳው ላይ ጠብቀኝ እናግርሃለሁ" አለችው። መክብብ "ዛሬ ባልና ሚስቱ ምን ነካቸው? በሆነ ባልሆነው ምን እናናግርህ ይሉኛል፣ እትዬም እንደ ጋሼ ቆጣ ቆጣ የሚሉ ከሆነ ጥያቸው ነው የምሄደው፣ የቢሮ ሥራ ነው እንጂ በዘመድ ወይም በጉቦ ካልሆነ ሲባል የምሰማው ግቢ ጠርጎ፣ ዕቃና የሰው ካልሲ አጥቦ ለመኖር የትም ሥራ እንደማላጣ ነው" እያለ እያወጣ እያወረደ እያለ "እሽ---- መክብብ ዛሬ በዚህ ቤት ሰላም ደፍርሶ ያለ መሰለኝ። አንተማ ሰላምታህንም አቀዝቅዘህብኛል፣ ለመሆኑ ምን ሆነህ ነው?" እራሱን አከክ አሸት እያደረገ ካንገቱ ጎንበስ ብሎ የወ/ሮ አረጋሽን ጥያቄ ከመመለሱ በፊት የገንረብሩክን ጥያቄዎች ለማስታወስ እየሞከረ ስለቆየባት

"በል እንጂ ትርሲትም አልቅሳ ነው የተኛችው፣ ምንድ ነው ነገሩ?" ስትለው፣ የትርሲት ስም በመጠራቱ ለንግግሩ መጀመሪያ ሆነለት

"አዎ እትዬ፣ እቤት ውስጥ ሲገባ ትርሲት እቃ ወድቆበት ነው ብዬ ልገባ ብሞክር አለወትሮው በሩ ከውስጥ ተቆልፏል። ምን ችግር ተፈጠረ ብዬ አሾልቄ ሳይ መታጠቢያ ቤቱ ውስጥ ስታለቅስ አየኋት። ከዚያ ትርሲትዬ፣ ትርሲትዬ እያልኩ ስጣራ እሷ ሳትሰማኝ ጋሼ ለምተው፣ መኖራቸውንም አላወኩ ነበር፣ ከመታጠቢያ ቤት ወጥተው ትንሽ ቆጣ አሉኝ። ትንሽ ቆየት ብለውም በቁጣ ጠርተውኝ ብዙ ጥያቄ ጠየቁኝ።"

"ደግሞ የቁጣ አጠራር ምንድን ነው ልጄ" ስትለው "እይ ማለቴ እርስዎ መክብብ፣ መኩ ሲሉኝ ለምሳሌ ደስ ይለኛል። እናቴ የጠራችኝ እየመሰለኝ። የዛሬውን ግን እትዬ፣ ጋሼ ምን እንደነካቸው አላውቅም ፤ሲጠሩኝ ልክ እንደውሻ ና! አንተ፣ አንተን እኮ ነው ሲሉኝ ውይ ጋሼ ጠሉኝ ማለት ነው ብዬ፣ እየፈራሁም፣ እየተናደድኩም፣ ነው ሩጬ የሄድኩት።"

እንዳሳት፣ ስለእስሪና ሰራተኛ ግንኙነት የተቻላትን ያክል ስማስታወስ እየሞከረች የተፈጠረውንም ግርግር መልክ መልክ ለማስያዝ ጥረት እያደረገች ሲሆን፣ ስነገሩ ወ/ሮ አረጋሽ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአስተዳደር ዲግሪዋን ካገኘች በሁዋላ በባንክ ቤት ውስጥ ለሰባት ዓመት በተለያዩ ክፍል ስትሠራ ብዙ የህይወት ተመክሮ አግኝታለች። በተለያዩ የስራ አጋጣሚዎች በአለቃና ሰራተኛ በሰራተኞችና በደንበኞች



መሃከል በተለያዩ ወቅቶች ችግሮች ተፈጥረው ብዙም ሳትደክም የመፍታት ልምዱ አላት ሌላው ቀርቶ መቺስ የውበቷ ነገርማ አይነሳ! እግዜር አስተካክሎ የፈጠራት ናት፣ አጋጣሚ ያመቻቸለት ለመጠየቅ፣ ያልተሳካለት በእንቅፋትና መኪናውን ያጋጨው እሷን እሷን ሲያይ ቤቱ ይቁጠረው! የቱጃሩ ብዛትማ ስንቱ ይቆጠር! ብዙ ባለሃብቶች ብር ስላላቸው ብቻ የፈለጉትን የሚያገኙ ስለሚመስላቸው አረጋሽን በገንዘብ ለመደለል መቺስ ያልሞከረ የለም። አረጋሽ ይህንን ሁሉ ሰው ሳታስቀይም ልዩ በሆነ ችሎታዋ ንጹህ ወንድሞቿ ያደረገቻቸው ብዙዎች ናቸው። ብዙ የሥራ ጓደኞቿ "ለአረጋሽ ጨመር ያለ ክፍያ ባንኩ መክፈል አለበት፣ እሷን ብሎ የሚመጣው ደንበኛ ቀልድ ነው እንዴ፣ እውቀትና ቁንጅና ሲገናኝ ጥቅሙ የትየለሌ ነው ይባል የለ" ይባባላሉ ።

"እኔ የምልህ ------ እናቴ ስትል የኔ እናት የኔን ስም ለማሞከሸት እይመችም እያሰች እሞካሽታኝ አታውቅም። በምትኩ የኔዋ አረጋሽ ነበር የምትለኝ። ለመሆኑ እናትህ በህይወት አሉ"?

"እዎ አሉኝ"

"አባትህስ ?"

"አይ እሱ እንኳን የስባት ዓመት ልጅ እያለሁ ነው የሞተው።"

"ውይ በጣም አዝናለሁ፣ ታስታውሳቸዋለህ?

"እዎ፣ አባቴ በስድስት ዓመቴ ማንበብና መጻፍ አስችሎኛል። ልዩ ብልሃተኛ፣ ከራሱ የበለጠ የሀገሩን

እድገት ይመኝ እንደነበረ ይነግረኛል። እናቴ እስካሁን የሱን ታሪክ ታጫውተኛለች።

"የሚገርም ነው፣ ለመሆኑ ምን ሆነው ሞቱ?

"ያኔ በቀይ ሽብር ጊዜ የኢሕአፓ አባላቶች ሲገደሉ እሱም ተገደለ" ገና ሲላት አጣምራው የነበረውን እግሯን እያፍታታች "በጄ" አለች ብዙ ለመስማት በመፈለግ። "ዩኒቨርሲቲ ተመርቆ ናዝሬት ገላውዲዎስ የሚባል ት/ቤት ነበር የሚያስተምረው ብላኛለች እናቴ። እሷም እኮ እስከ 12ኛ ክፍል ተምራለች። አባታችን ሲሞት እኔንና ወንድሜን ይዛ ሌላ አማራጭ ስሌለላት ሸንኮራ እናትና አባቷ ጋ ይዛኝ ገባች። እናትና አባቷም ትምህርት ቤት በሄድን ቁጥር ደስተኛ አልነበሩም። 'ተምሮ ለመሞት ነው? አባታችሁ ቢኖር እንኳን ኢትዮጵያን ዓለምን ይመራ ነበር፤ ዝናው እስካሁን አለ፡ ጎበዝ ነበር፣ ታዲያ ምን ዋጋ አለው? ጉብዝናውና ማወቁ አስገደለው። እኛ እስካሁን የኖርነው ለመጣው ገዥ ነኝ ባይ የታዘዝነውን ሁሉ እሺ በማለታችንና ፖለቲካን በመፍራታችን ነው' እያሉን ሁልጊዜ ስለሚያስፈራሩን ሁለታችንም ትምህርታችንን አቁመን ግብርናችንን ተያያዝነው። በዛሬው ግዜማ እትዬ የግብርናን ነገር እኮ ብታዩት ቢወጣ ቢወረድ ሌት ተቀን ቢደከም ጠብ የሚል ነገር የለም። ሆነም ቀረ እከተማ ደህና ዘመድ ያለው ገበሬ ቢያንስ የማዳበሪያውን እዳ ከተከፈለለት፡ ያመረተውን ለእጻ ካልሸጠ ካመት ዓመት ልብስ መቀየር ቢቀርም ብዙ ሳይራብ ይደርሳል።"



ወ/ሮ አረጋሽ አቋረጠችውና "እሽ" ብላ ዓመታት ወደኋላ ተመልሰች፤ ስለታላቅ እህቷና ወንድሟን በማሰብ በድንገት እንዚያ በተፈጥሮ የተኳኳሉ የሚመስሉ፡ ዕይኖቿ በእንባ ተወጠሩ፡ የደም ሥሮቿ ተግተረተሩ፡ ቸርቸር ጎዳና ላይ ሬሳዋ ተጥሎ የተገኘው እህቷ፡ በዘይት የተጠበሰው ወንድሟ፡ የሰፈሩ ጎበዝ ተማሪዎች ሁሉ እንዴት እንደተገደሉና በእስር እንደተሰቃዩ ትዝ ብለዋት እንባዋን መቆጣጠር አቅቷት ለቀቀችው። የመክብብ አባት፡ ከእህትና ወንድሟ ጋር ይተዋወቁ ይሆናልም ብላ አሰበች። ቀና ብላ መክብብን አይታ "አይዞህ የኔ ጌታ አለሁልህ" ስትለው መክብብም የወ/ሮ አረጋሽን ሁኔታ አይቶ እምባው ከየት መጣ ከየት ሳይባል ያወርደው ጀመረ። በውድቅት ሌሊት አበረንዳ ላይ ተቀምጠ ያልታሰበ እምባ፡ ያነቡ ጀመር። "በል ፊትህን ታጠብና ተመለስ" ብላ እሷም ልትታጠብ ገባች።

"ምን ያለበት ዝላይ አይችልም" እንደሚባለው በድንገት ገብረብሩክ "ምንድን ነው የምታንጎዳጉጂው፡ እትተኛም እንዴ?" አለ፡ በደም የቆሸሹ ልብሶቹን እየፈተሸች መለሉት። ወ/ሮ አረጋሽ ቀልዶቿ በአብዛኛው መልእክት አላቸው። "ማንኛውም ቀልድ ትንሽ እውነታ አለው" ይባል የለ!! "እሺ ገብርዬ፡ ምነው አርፈህ ብትተኛ" አለችው። የትርሲት ቅዠት ትዝ ብሏት። "አይ ነገርኩሽ ብትተኚ ይሻላል" ብሎ ቆጣ ሲል "የእናንተ ነገር ሌላው ቢቀር የመተኛት ወይም ያለመተኛት መብት የለንም እንዴ?" ብላ ጀርባውን መታ መታ አድርጋ

ፈገግ አለችለት። አድርጋው የማታውቀው ማምሸት ገብረብሩክን ገርሞት እንደገና ተመልሶ መተኛት ተሳነው።

ገና ወደ በረንዳው ስትወጣ መክብብ እየጠበቃት ነው። ጨረቃዋና የበረንዳው መብራት ዳጎስ ያለ ሰውነቱን የባሰ አሳምረውታል። የቁመና ነገር ሲነሳ፣ የኑሮ ጉዳይ፣ የእድል ጉዳይ ሆነና ነው እንጂ ማታ ማታ ወደ ት/ቤት ሲሄድ ባለችው ተሽቀርቅሮ ላየው ገብረብሩክ ዘበኛ መክብብ ባለቤት ነው የሚመስሉት።

"በል ቅድም የጀመርክልኝን ጨርስልኝ፣ በሩን ማን ቆለፈው?"

"እኔ እንጃ፣ እሱን ማን እንደቆለፈው"

"አንተን ለምን ተቆጣህ?"

"ትርሲት ምን ሆነች ብዬ በሩ በመዘጋቱ በመሰኮት በማየቴ ነው መሰለኝ።"

"ምንድን ነው የጠየቀህ?"

"የተንጓጓበትን ቦታ እያወቅህ እንዴት አላውቅም ትለኛለህ? በቃ እንዲህ ነው እትዬ።"

"እውነትህን ነው! ይብቃን፣ ድንገት ነገ ምን አወራችሁ ቢልህ ትምህርቴን ማታ ማታ ሳላቋርጥ እንድማር ነው ስትመክረኝ የነበረው በለው። በል ደህና እደር" ተባብለው ወደ መኝታ ቤታቸው አመሩ።"

መንጋት አይቀር ነጋ። ትርሲት ወደ መታጠቢያ ቤት ለመሄድ መራመድ ስትጀምር እግሯ ተሳስሮ ቁጭ አለች። ለነገሩማ እንኳን ክብረ ንጽህናን በጉልበት መወሰድ ቀርቶ ክብረ-ንጽህና የሌላቸውን እህቶች በጉልበት መገናኘት



መራመድ ብቻ ሳይሆን ሊላም የጤና ችግር ያመጣል። እንደምንም ተቆጣጥራ ተመልሳ ተኛች፣ ወደ ሥራ አስኪሄዱላት። ወ/ሮ አረጋሽ እንደነቃች የሮጠችው ወደ ትርሲት መኝታ ቤት ነበር። ልትቀሰቅሳት ብትሞክር ጸጥ ረጭ አለችባት። ክው አለች። "ትርሲት፣ ትርሲት" ብላ ብትነካካትም ምንም መልስ አጣች። ተደናግጣ "ገብርዬ፣ እስቲ ና ጉድ እንዳንሆን ቶሎ ወደ ሃኪም ቤት እንውሰዳት" ስትለው ገስጥ አድርጎ ሲያያት አቅም ቢኖራት ዘላ ብታንቀው እየተመኘች ህይኗን በመጠኑ ገለጥ አድርጋ ስታየው "አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም" ተብሏል ብሎ ሊተርትባት ካሰ በኋላ የባሰቤቱን ትገዘብት ፈርቶ ዋጥ አደረገው። ትርሲት ወ/ሮ አረጋሽን "እትዬ እንቅልፌን ስላልጨረስኩ ነው ደህና ነኝ" ብላ እስኪወጡላት እንደገና ተቅልል እለች።

ቁርሳቸውን በልተው ሲወጡ "መኩ በል ትርሲትን አመም ስላደረጋት ዛሬ ያንተ ተራ ነው። የምትፈልገውን ቁርስ አቅርብላት" ብላ ተከታትለው ወጡ። ከአንድ እንጀት እንደወጡ የሚያዩት ትርሲት ትናንትና እንደዚያ እንጻቀረቀረች ሳይናገራት በመተኛቷ ብዙም ሰላማዊ እንቅልፍ ሳይተኛ ነው ያደረው። እንደ እህትና ወንድም መተያየት ብቻ ሳይሆን የማያወሩት፣ የማይወያዩት እንዳቸው ካንዳቸው የሚደብቁት ምንም ነገር የለም። ት/ቤት ስትሄድም ስትመጣም ሸኚም ተቀባይም እሱ ብቻ ነው።

ብዙም ሳይቆይ ወደ ክፍሏ ሄዶ ቀስ ብሎ "ትርሲት፣ ትርሲትዬ" ሲል "መክብቤ እሰማሃለሁ" ብላ እያሰቀሰች እጇን ዘርግታ ‹‹ደግፋኝ›› ስትለው ደገፍ አድርጎ እንዳቆማት ገና

መራመድ ስትጀምር "ዋይ እናቴ፡ ዋይ እማዬ" ብላ እምባዋን ስትለቀው በሁኔታው በጣም ተደናግጠ ወደ አጠገቡ ጠጋ አድርጎ እምባዋን በጃኬቱ ጠራረገላት::

"ወይኔ መክብብዬ፡ በታአምር መራመድ አልችልም፡ ታቀፈኝና መታጠቢያ ቤት አድርሰኝ" ስትሰው እንክብክቦ ወሰዳት:: ትንሽ ቆይታ እየጮኸች "መክብቤ በእናትህ ከዚህ ውስጥ አውጣኝ፡ እዚህ መታጠቢያ ቤት ከምጠቀም በአቅም ማጣት መጸዳጃ ቤት እንደሌላቸው ሌሎች ወገኖቻችን በየሜዳው ብጸዳዳ ይሻለኛል" እያለች ሲታቀፋት "መክብቤ እግሬን..እግሬን አትጫነው፡ አታንቀሳቅሰው፡ እሁሁሁ..." ስትለው እሱም እምባውን እየጠራረገ "ትርሲትዬ ለካ ትናንት የተንጓጓው አንቺ ስትወድቂ ኖሯል እንዴ? የሚገርም ነገር ነው:: ጋሼ እኔ ላይ ከሚጮሁ ለምን ሃኪም ቤት አይወስዱሽም ነበር?"

"ልውሰድሽም ቢለኝ ድብን ልበል እንጂ ከሱ ጋር አልሄድም ነበር::"

"ምነው ምን አደረገሽ?"

"ተወኝ ይቅርብህ፡ ምንም አይሠራልህም" ብላ መሸፋፈን እየሞከረች ሳለች "እሽ ለእትዬስ ለምን ውስዱኝ አትያቸውም ነበር? እትዬ እኮ በጣም ጥሩ ሰው፤ የሰው ችግር የሚገባቸው ናቸው:: ማታ እኮ ያን የነገርኩሽን የቤተሰቤን ነገር፡ በተለይ የአባቴን ነገር ስነግራቸው አብረን ስናለቅስ ነው ያመሸነው:: 'አይዞህ አለሁልህ' እያሉ ሲያባብሉኝ አባቴን ያውቁት ይሆን? ወይንስ ዘመዱ ይሆኑ? ብቻ ምኑ ቅጡ ልበልሽ ብዙ ነገር ሳሰላስል ነው ያደርኩት::"



"አይ መክብቤ፡ እንዳልከው እትዬ ለሰው አዛኝ፡ የማይዋሹ፡ ለሰው ሲቆረቆሩ ተወዳዳሪ የሌላቸው ናቸው:: ይሄ እንኳን ባላቸው እግራቸውንም አጣቢ መሆን የሌለበት ሰው ነበረ::"

"እንዴት ትርሲትዬ፡ ጋሼን አንቱ አደልም እንዴ የምትያቸው? "

"አንተ ደግሞ እስካሁንም አንቱ ያልኩት ማንነቱን ለማወቄ ነው::"

መክብብ ሁኔታዋ ግርም ብሎት "በጣም ነው የገረምሽኝ፡ ከእኔ ከወንድምሽ የሚያስደብቅሽ ምን ነገር ተፈጠረ?" ሲላት "ቆይ ላስብበት አትቸኩል" እንዳለችው ቁርሷን እያዘገጀች ስለሷ ማሰቡን አላቆመም:: "ጋሼ ትናንት በኔ ላይ እንደዚያ የጮኹት እቃ ሠብሬ ይሆን? ስታለቅስም አይቻለሁ" ይላል ብቻውን::

ቁርሱን እያቀረበ "ትናንት እኮ ግድግዳው ሲንጓጓ ምን ሆንሽ ብዬ ልገባ ብዬ በሩ ከውስጥ ተዘግቶብኝ የማደርገው ግራገብቶኝ ስሯሯጥ አቀርቅረሽ ስታለቅሽ በመስኮት አይቼሽ ስጠራሽ አንቺ ሳትሰሚኝ ጋሼ ስምተውኝ ወጥተው ሲነዘንዙኝ ነው ያመሹት"

"ደግሞ አንተን ምን ሁን ነው የሚልህ?"

"ስንቱን ልንገርሽ፡ የተንጓጓው የት እንደሆነ ታውቃለህ? ምን ፈልገህ ነበር በመስኮት ስትንጠለጠል የነበረው? ምንትሴ ሲሉኝ ነበረ::"

"ህ! ሥራውን ስለሚያውቅ ነዋ! ይኼ ግፈኛ..."

"ኧረ እባክሽ አንቺ ልጅ እንደዚህ አታስጨንቂኝ! ነው ወይስ ከጋሼ ጋር ተጣልታችሁ ነበረ? "አሽ መታኝ ብልህ ምን ታደርግልኛለህ?"

"ሆሆይ ..ባለጊዜ ናቸው ይባል የለ! እንዴ አንድ ነገር ቢያደርጉኝ ወይ ቢያስደርጉኝስ?

ለእኔ የሚጠቅመኝ ከሆነ ምንስ ብታደርግልኝ ያስፈራሃል ማለት ነው?

እሺ አንችን የሚያስደስትሽን ነገር ሁሉ ለማድረግ ከጎንሽ ነኝ

"እየሀ እንዲህ ነው ወዳጅ"

"ታዲያ አንቺ እህትሽ ጋር ስትሄጂ እኔንም ትወስጂኛለሽ::"

"ወይ መክብቤ፣ ሂጂ ነው፤ መቶ በመቶ እርግጠኛ ነኝ እንደምወስድህ::"

"እና መተውሽ ነው አይደል?"

"ምነው መክብቤ፣ አታቻኩለኝ" ስትለው "እሽ እንዳልሽ" ብሎ ጉድ ጉድ ማለቱን ቀጠለ::

ስልክ ደጋግሞ ይጮሃል:: ከብዙ ጥሪ በሁዋላ መክብብ ከውጭ መጥቶ አንስቶ ለትርሲት ሲሰጣት፣ "ከውጭ ነው?" አለቺው:: በምልክት የእምቢታ ምልክት አሳይታው ተሸፋፍና ተኛች::

"ጋሼ ተኝታለች!" አለ እየፈራ እየቸረ::

"አንተ ጨምላቃ ስትንሾካሾክ የማልሰማህ መሰለህ! ስጣት ብዬሃለሁ!"



መክብብ በንዴት "ትርሲትዬ ብታናግሪ ይሻላል" ብሎ ሲወረውርላት "እህ.." ብላ አቤት አለች:: "ትስሚያለሽ ህይወትሽን እንዳታበላሺ. የምታደርጊውን ሻጥር ብታቆሚ ይሻላል:: ማታ ሆን ብለሽ ቅዠት አስመስለሽ ስሜን ስትጠሪ አረጋሽ ለምታ አስሬ እየደወለች ምን አድርገሃት ነው? በድንጋጤ ስትቃዥ ያደረችው ብላኝ ሳስፈራራት መልስ ስትሰጠኝ ተናድጄ ገፋ አድርጌያት ነው ብያታለሁ:: ስትጠይቅሽ ከዚህ በላይ ባትቀባጥሪ ጥሩ ነው:: ነገሮችን ማበላሸት ካሽፈለግሽ፣ ይገባሻል? አለና ስልኩ ተዘጋ::

ከብዙ ነገሮች ሁሉ ተምታቶባት ለውየውም 'ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮኻል' ሆነባት:: ማስፈራራት፣ ማስፈራራት .. ሃሳብ እንዲሁ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስውን የሚሸሻል? ያ ብርቱካን የመሰለ ፊት እየተቀየረ ያ ፈገግታ ሲጠፋ ብቻ ምኑ ቅጡ ብዙ ለውጥ አላት፣ ጥውልግልግ ማለት ጀምራለች::

"መክብቤ በቃ አኩረፍከኝ ማለት ነው?"

"ወይ ትርሲትዬ፣ ምን አድርገሽኝ፣ ይልቁንስ መለስ አለለሽ? ሲላት እጁን ይዛ ስጥቂት ጊዜ አሰበችና "መክብቤ እስካሁን ከነገርኩህ ሚስጥር በጣም ከባድ ሚስጥር ነው የምነግርህ!"

"ግድ የለሽም አቡዬን" ብሎ ሲምልላት ሳቅ አያለች

"አቦይ ብለህ በትግርኛ ቋንቋ እየቀለድክ ነው?

"ውይ አይደለም፣ ሽንኩራ ውስጥ ያሉትን የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያንን ነው አቡዬን ብለን የምንምልባቸው"

"እሺ እና ሚስጥር እጠብቃለሁ ነው የምትለው? "

"ሰለሱ አታስቢ፤ የሚጠቅምሽ ወይም የሚጠቅመኝ ካልመሰለሽ ባትነግሪኝ ግድ የለኝም፤ ሚስጥር እኮ የአደራ እቃ ወይም ገንዘብ ነው:: ሰው በአደራ ያስቀመጥብሽን ን ብረት ለሌላ ሰው ይሰጣል እንዴ?" እንዳላት

"አይደለም፤ ላንተማ መንገር አለብኝ" ብላ ከምን እንደምትጀምር ስታስብ ሌላ ስልክ አቃጨለ:: ወ/ሮ እረጋሽ ነበረች::

"እመት፡ ትርሲት" አለች፡ ወ/ሮ እረጋሽ ጠርታት የማታውቀውን አጠራር በመጥራቷ እየገረማት "ለመሆኑ አሁንም እንደተኛሽ ነው? አየሽ እኛ ከዘመዶችሽ አለያይተን ከእህትሽ ጋር እንድትገናኝ የምናደርገውን ጥረት እንኳ የ20 ዓመት የ5 ዓመትም ልጅ ይረዳዋል:: ታዲያ ይህንን ሁሉ ድካማችንን መና እንዳይቀር ከአባትሽም ጋር እንዳንቆራረጥ ካንቺ በኩልም ጥረት መደረግ አለበት::"

"እሺ እትዬ፣ እኔ ከእርስዎ ቃል አልወጣም::"

"አይደለም ቆይ እስጨርሽኝ፣ እኔን እንደምታከብሪኝ ገብረብሩክንም ማክበር አለብሽ:: እኔ እንኳን የማልመልሰለትን መልስ አንቺ መናገር የለብሽም:: ገብረብሩክን እንዳባትሽ እይው እንጂ እንደ ከንፈር ጓደኛሽ ማየትም፣ መመኘትም የለብሽም:: ሌላውን ሌላ ጊዜ አስረዳሻለሁ፣ ተረዳሽኝ በሚገባ? ቁርስሽን በላሽ ለመሆኑ? በይ ወደ ሥራ መመለስ አለብኝ፣ ለማንኛውም እስቢበት፤ ብላ ስልኩን እንደዘጋች ሆሆይ፣ እንዳንዴ እኮ ቀበጥ ያደርገኛል፤ የአንድን ወገን ሀሳብ ብቻ



ተቀብዬ በዚች ምስኪን ላይ ወረድኩባት ይቅር ይበለኝ እቴ ስትል ከህሳቧ ባነነች::

ትርሲት በትምህርት ጉብዝናና በውበቷ ምስራቅ እጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጣት መጠቋቆሚያ ነበረች:: ከወ/ሮ አረጋሽ ንግግር 'ገብረብሩክን በሌላ አትይው' የሚለው 'ከጅላኛለች' ብሎ እንደነገራት ለመረዳት ጊዜም አልፈጀባትም:: አሁን በተለይ በሃሳብም በምንም እንዲረዳት ለመክብብ ታሪኩን ለማማከር ቆርጣለች:: መከብብ በበኩሉ በሃሳብ ይዋልላል:: "ምን ልትለኝ ይሆን? መቸስ ወደድኩህ እንደማይወጣት ነው፤ እኔ 26 እሷ 20 ዓመት፤ እሷ 12ኛ የጨረሰችና ለዩኒቨርሲቲ የተዘጋጀች፤ እኔ 12ኛ ክፍል" ብሎ ተከዝ አለና እንደ ግጥም ብጤ "አያሳካም እንጂ ቢሆንማ ኖሮ .. "ብሎ ጀመረና "ውይ ሰይጣን ነው የገባኝ እህቴ እኮ ነች" አለና "ምን ይሆን ጋሼን ደብድብልኝ ልትል ይሆን?" የመሳሰሉትን የሃሳብ አይነቶች ያነሳል ይጥላል::

"መክብቤ ስልኩን ጨርሻለሁ" ብላ ጠራችው:: "እሽ" ብሎ ሮጦ ገባ:: "እኔ እምልህ ያቺ የነገርከኝ የመጀመሪያ ገርል ፍሬንድህ ግንኙነት ስታደርጉ ክብረ ንጽህና ነበራት እንዴ?

"ረስተሽው ይሆናል እንጂ ነግሬሽ ነበረ:: በጣም ጨዋ ሃይማኖተኛ ነበረች እኮ፤ "

"አንተ ደግሞ የነሱን ነገር እንኳ ተወው፣ ሀይማኖተኞች ነን እያሉ ፖስተካው፣ መዳራቱ፣ ንግዱ፣ የሃይማኖት ትምህርት ሊያስተምር በሚል ሰበብ ወደ

አውሮፓና አሜሪካ ቪዛ መንገዱ፣ ..ምን የማይሰሩት ነገር አላቸውና!"

"መዳራትን በተመለከተ እንኳ አጉል ተጋኖ ተወራ እንጂ ሁሉም በየሃይማኖቱ ተዋዶ መጋባት ያለ ነው:: በእርግጥ ፖለቲካ ስላልሽው ጉዳይ ሃይማኖትን ለፖለቲካ መሳሪያነት መጠቀም ከዚህ በፊትም የነበረ፣ ወደፊትም በተራቀቀ መልኩ የሚኖር ነው::"

"ሳቅ እያለች፣ በጣም ጥሩ፤ ወደእኔው እየተጠጋህ ነው:: ቤተ ክርስቲያን እየተመላለሰ መስቀል ለመሳለም የሚሻማ፣ አንገቱ ላይ መስቀል ያንጠለጠለ ሁሉ ጨዋና ታማኝ እንዳልሆነ መዘንጋት የለብህም:: ቤተ ክርስቲያን ሄደው የማያውቁ፣ ያልዘመሩ ችግር አለባቸው እንደማትለኝ ተስፋ አደርጋለሁ:: ለመሆኑ ምን ያህሉ ሕዝባችን ይመስልሃል ከአሥርቱ ቃላት ትእዛዝ ሦስቱን እንኳን በትክክል የሚፈጽመው? ተወኝ አባክህ ወደ ጨዋታችን እንመለስ!"

"ልክ ነሽ፤ ሌላም ሰው አሁን የነካካሻቸውን ነጥቦች አብራርቶልኝ ያውቃል:: እንዳልሽው እጄን እየለጠሁ ነው:: እናማ ይኸውልሽ ያቺን ጓደኛዬን ከነክብሯ ነበር ያገኘሁዋት:: "

"ከሆነስ በሁዋላ አላመማትም?"

"እሱማ የት ይቀራል፤ ለብ ባለ ውሃ መታጠብና መንከር ጥሩ ነው ብለውን አደረግን:: በማግስቱ እሽክም እለች እልሻለሁ:: ገንዘብ ካለማ መድሃኒት ቤቶቹ ካነጋገርቸው መድሃኒት ይሰጣሉ አሉ::"



"እና መክብቤ፣ ትናንት ይህ አረመኔ እንተ ላይ የጮኸው.." ብላ እጉልበቱ ላይ ድፍት አለችና ተንሰቅስቃ እያለቀሰች እንባዋን ታወርደው ጀመር:: ቀና እደረጋትና፣ "ምነው ትርሲትዬ፣ አንቺ እኮ ገና ብዙ ተስፋ ያለሽ ነሽ፤ በሆነ ባልሆነው እያለቀስሽ እራስሽን መጉዳትን ጤናሽን ማቃወስ የለብሽም::"

"ጤናዬንማ ይሄ ጭራቅ ሰውዬ እቃወሰው:: ያን ጊዜ የተንጓጓው እኮ በግድ አንቆ እፌን እፍኖ ክብሬን ሲወስደው ነው" ስትለው [redacted] ሚካኤል ኸረ ያንተ ያለህ! ጋሼ አንቺን? እግዚኦ! በስመ እብ" ብሎ አቅፎ እሻሻት:: "እይዞሽ የእኔ እህት ሁሉም ያልፋል" ብሎ እንዳቀፋት ለጥቂት ጊዜ ቆዩ::

# ምዕራፍ ሁለት

ወ/ሮ አረጋሽና ገብረብሩክ የሰሞኑ ወሬያቸው በሙሉ የትርሲትን የቪዛ ጉዳይ እፋጥነው ወደ ጀርመን መላክ ስለሆነ ፓስፖርት የምታገኝበትን መንገድ አመቻችተዋል:: ገብረብሩክ የቀጠና ሰለት የደህንነት ሃላፊ ስለሆነ በዚያ ሥልጣኑ በመጠቀም ከ12 ቀበሌ መታወቂያ ሊያወጣ የተለያዩ ስልቶችን እጠናቋል:: እግረመንገዱንም ለትኬቷ መግዣ ለራሱም ለምኑም ለምኑም የአቶ እምባዬን ሹራብ ቤት ከነማሽኑ ቁልፉን ለመሸጥ እየተሯሯጠ ነው:: ውክልና ይኑረው እንጂ ለሙ እስካሁን በአቶ እምባዬ ነው:: ስሙን በራሱ አዛውሮ

ለመሸጥ ገንዘቡንና ጊዜውን እየከለከለ ነው:: ገብሬይ የሚባል ውስጠ ሚሰጥሩን የሚያውቅ ገብረብሩክን በዓይነ ቁራኛ እየተከታተለው ነው::

መክብብ በአጭር ጊዜ ውስጥ መድሃኒቱንም፣ ምክሩንም ብሎ ትርሲትን ወደ ድሮዋ እየመሰሳት ነው:: እሷም በመክብብ፣ መክብብም በትርሲት መማል ብቻ ነው የቀራቸው:: ገብረብሩክ የአነሱን መቀራረብ ወዶታል:: ትርሲት አንድ ነገር እንኳን ብትሆን በመክብብ ለማሳበብ ነጋ ጠባ ለ/ወ/ሮ አረጋሽ እያቀነባበረ ያቀርባል:: "ትስሚኝ አለሽ? የአነዚህ ልጆች ሁኔታ አላማረኝም፣ አንዳንዴ ቆጣ ብትያቸው ይሻላል:: አኔ የእድል ነገር ሆኖብኝ ብቆጣም አያምርብኝም:: ባለፈው እንደ አባት ነኝ ብዬ ብቆጣ የተፈጠረውን ሁኔታ ታውቂያለሽ:: ለማንኛውም አስቢበት" ይላታል::

ወ/ሮ አረጋሽ የመክብብን ሁኔታ ሳታሰብ ያደረችበት ቀን የለም:: ዛሬ አመቺ ቀን ሆኖላት ገብረብሩክ ሰብሰባ ሰላለኝ ቢያንስ እስክ ሌሊቱ ሰባት ሰዓት አመሻለሁ" ስላላት የቤታቸውን ጣጣ ከጨረሱ በኋላ ትርሲትም ደከመኝ ብላ ተኝታለች::

" መክብብ አስቲ ና ትንሽ አጫውተኝ::" ስትለው

እመት እትዬ ብሎ ከበረንዳው ወደ ውስጥ አንደገባ

እሺ! ትምህርት እንዴት ነው? ዘንድሮም ፫ኛ ነው የወጣኸው?"

"ምን ችግር አለና፣ ደግሞ ለማታ ትምህርት፣ ትርሲትም በደንብ ስለምታስጠናኝ ሁሉም ነገር ቅልል ነው የሚለኝ::"



"በቃ ትርሲትን በዚያው ተላመዳት:: በደምብ ደግሼ ነው የምድርህ::"

"እሱማ በምን እድሌ ነበር:: ግን እንደ እህትና ወንድም እኮ ነው የምንተያየው:: ፍጹም እህቴ ነች እኮ" አያለ ሳይጨርሰ ማምረሩ ገባትና "እኔም እኮ ታላቅ እህትህ ነኝ፡ ሰው ከወንድሙ ጋር መቀለድ አይቻልም እንዴ?" ብላ ወሬውን ለመቀየር ሞከረች:: አይዞህ ብዙ ነገር እየተመካከርን እህትና ወንድም ሆነን እንኖራለን::" በል እንዳልኩህ አታስብ ደህና እደር::"

ቀናቶች ሳይታሰቡ እልም ጭልጥ ይላሱ ትርሲት በድንገት፣ "መክብቤ" አሰች በጥዋት ወደ ተኛበት አየተጠጋች::

"እንደምን አደርሽ፣ ምነው በጥዋት?"

"አይ ደህና ነኝ:: አልነገርኩህም እንጂ ትላንትና ዛሬ ዝም ብሎ ቋቅ ይለኛል"

"አይዞሽ! እንዴት ነው? ወደ መጸዳጃ ቤትስ ቶሎ ቶሎ ያስሄድሻል? "

"እንዲያውም፣ ወደላይ ብቻ ነው የሚለኝ:: ሰአህቴም ያንን ነገር አፍረጥርጬ ነገርኳት" ስትለው "አይ፣ ባትነግሪያት ጥሩ ነበር:: በሰው አገር እንዳታስጨንቂያት ብዬ ነው::"

"ብነግራትም እኮ እድሜ ላንተ በጣም ደህና እንደሆንኩ ነግሬያታለሁ:: ያንተንማ ውለታ እኛ ባንከፍለው ሰአንተም አይዞህ ባይ ይዘዝልህ ብላሃለች:: የሚገርምህ ይሄ ጭራቅ ብቻዬን እንዳያገኘኝ የፈጠርነውን ዘዴ ስነግራት አድንቃ አድንቃ አልጠገበችውም" ብላው ወደ መኝታ ክፍሏ

ተመልሳ ጋደም እንዳለች ገብረብሩክን ወደ ሥራ ለመሄድ ተፍ ተፍ እያለ:: በድንገት በሯን ብርግድ አድርጎ ያውልሽ መታወቂያሽ ሜግሬሽን ሂጅና ስላስ ጋ ብለሽ ግቢ:: ሁሉንም ነገር አስረድቻቸዋለሁ፣ ጨርሽና ቶሎ ተመለሽ:: "ትርሲት ገብረብሩክ" ትላለች አዲሱን መታወቂያዋን ደግማ ደጋግማ እያነበበች:: ለጥቂት ደቂቃዎች ጸጥ አለችና ወዲያውኑ "እባክህ እምላኬ ትእግስቱን ስጠኝ" ብላ ተማጸነች:: እንዳንዴም አቶ እምባዬ 'ምነው እኔ አባትሽ በህይወት እያለሁ በዚህ በከሃዲ ሰው ስም የምትጠሪው" ያሏት እየመሰላት ክው ብላ ትደነግጣለች::

ወ/ሮ አረጋሽ በድንገት ብቅ ብላ "እናንተ ልጆች ባሌን አቃጥላችሁ ልትገድሉብኝ ነው እንዴ?" እያለች ስትስቅ "ወይ እትዬ ምን አጠፋን?"

"ወቸ ጉድ የዛሬውንስ ያንተ ነው፣ ሲያየኝ ደንገጥ እንኩዋን ብሎ ከመቀመጫው አልተነሳልኝም ተብለህ ነው የተከሰስከው: ምነው መክብብ! ገብረብሩክ እኮ አባወራ ነው:: በዚያ ላይ አክብሩኝ፣ ሆይ ሆይ በሉኝ የሚወድ ነው:: ለማንኛውም አደራህን ቢቆጣህ እንኳን እንዳታማርር!"

"ምንም ችግር የለም፣ በሱ በኩል አያስቡ" ብሎ አስደሰታትና ማውጣት ማውረዱን ቀጠለ:: በተለይ ትርሲትን እንደገና አስገድዶ ለመድፈር እንዳይችል የእሱ መኖር ስላገደው ሊያባርረው እንደሚያስብ ስለገባው መፍትሄ ፍለጋ ከራሱ ጋር ሙግት ገጥሟል::



ሁለቱንም በጣም ያስጨነቃቸው ግን ለወ/ሮ አረጋሽ እንዴት እንደሚነግሯት እና ከዚያ በኋላስ የት እንደሚኖሩ የትርሲት የጉዞ ሁኔታ እንዳይደናቀፍ የመሳሰሉት ናቸው::

"ስልክ ይፈልግሃል መክብቤ፣ እትዬ ናቸው"

"ስማ፣ ትንሽ ያበዛኸው መሰለኝ::"

"ምነው እትዬ?"

"ገብረብሩክ ስላንተ ብዙ ነገር ሲነግረኝ እንዲያው ዝም ብለህ ጠልቶኸው ነው እያልኩ እፍ እፉን ነበር የምለው:: አሁን ግን በጣም ከምናምነው ከኔም ከገብረብሩክም ጓደኛ ከሆነ ሰው ነው የሰማነው::

"ወቸ ጉድ! ለመሆኑ ምናለ እሉኝ እትዬ!"

"ብዙ ነገር ነው ብቻ በጣም ነው የማዝነው:: እይዞህ! እንደ ታናሽ ወንድሜ ነው የማይህ፣ ብዙ ሚስጥር ይኖረናል እየተባባልን አንተ ግን ከትርሲት ጋር የሠራችሁትን እንኳ ደብቀኸኛል::"

"ደሞ ምን አደረግን፣ እትዬ?"

"አንተ ደግሞ ልብህ እያወቀው ለኛ ወዳጅ ያደረከውን ነግረኸው ለኔ ግን ደበከኝ:: ስሱ ከምትነግረው ለኔ እትዬ ተሳስተን ወይም ተመካከረን የትርሲትን ክብረ ንጽህና ወሰድኩ ብትል ምንም አላደርግህም ነበር" ብላ ገና ሳትጨርስ "እረ ወዴት ወዴት፣ ኧረ የምን በሰው ላከክ" ሲል "አንተ ስንት ዘመን አብረን የኖርነውን ሰውዬ ዋሸ ልትለው ነው?"

መክብብ ትእግስቱ ተሟጥጦ "እትዬ እውነቱን ልንገርዎት፣ እዚህ ቤት ያለሁት እርስዎና ትርሲትን ብዬ ነው::

እርስዎም ከተለወጡብኝ ሌላ ምን አማራጭ አለኝ:: ኑና አስናብቱኝ:: ወይም አሁኑኑ ውጣ ካሉኝም መሄድ እችላለሁ::

ወ/ሮ አረጋሽም ከው አለች:: " መኪ፥ ውጣ የሚል ቃል መጣኝ? ስማኝ አንድ ሃሳብ መጣልኝ ሁኔታውን በደንብ እስከማጣራ የትም እንዳትንቀሳቀስ፤ ብትሄድም በደንቡ ነው የምሸኝህ:: በውጭም እንድንጠያየቅ:: በል ወደ ሥራ ልመለስ::

"ትርሲትዬ ጉድ ሰማሽ? ይኸ ደቃቃ ሰውዬ ነገር እያቀነባበረ ከእትዬ ጋር እያቃቃረን ነው:: "

"እይ መክብቤ እኔም እኮ ብዙውን አልነገርኩሁም:: እትዬ በኔም ላይ ብዙ ለውጥ እያሳዩ ነው:: በዚህ እይነት ያንን ነገር ብንነግራቸው ሊያምኑን አይችሉም::"

ገብረብሩክ ከየት መጣ ከየት ሳይባል መኪናውን ጓ እድርጎ ዘግቶ እንደገባ "ነይለቲ አንቺ፥ ፓስፖርትና መታወቂያሽን ያዥና" ሲላት ካስቀመጠችበት አውጥታ ስትጠጋው ምንጭቅ አድርጎ፥ የቻለውን ያህል ብጭቅጭቅ አድርጎ በራሷ አባት ስም ያወጣላትን መታወቂያና ፓስፖርት "እንደምታደርጊ አድርጊ" ብሎ ወርውሮላት "ላንቺና ለቤተሰቦችሽ ስል ከማልወጣበት ማጥ ውስጥ እየገባሁ ነው" እያለ እየተልጎመጎመ ወጣ::

ገብሬ-ይ ከገብረብሩክ በተሻለ ከባለሥልጣኖች ጋር ግንኙነት ስላለው በአቶ አምባዬ ንብረት ላይ የሚያደርገውን ሁሉ ለማወቅ ብዙም አልተቸገረም:: ሌላው ቀርቶ ልጃቸውን እንደ ልጁ አድርጎ መታወቂያና ፓስፖርት አውጥቶ ጀርመን



ሊልካት እንደሚንጎዳጎድ ደርሶበት ስጀርመን እምባሲ ደብዳቤ አጽፎበታል::

"ሃሎ አረጋሽ፥ ሃሎ፥ ሃሎ!?"

"ቆይ እንጂ ገብረብሩክ ቀስ በል፤ መክብብ ምኑን አውቆት ነው የሚጠቀመው፤ ወይ ገብረብሩክ ይህንንስ አያደርግም"

"ተይ እንጂ አረጋሽ፥ አቤት ውስጥ እኮ ምንም ሥራ አይሠሩም:: እኛን ሲያሙና ሲንሾካሾኩ ነው የሚውሉት::"

"ገብረብሩክ፥ ትርሲትን ልደውልላትና ደግሜ እደውልልሃለሁ::"

"ለሚኝ አረጋሽ፥ ወዲያ ወዲህ ማለት አያስፈልግም:: እኛን ለምን ትጥላን፥ መክብብ እድሷን እንዳበላሸው ንገሪያት"

ምነው ገብሬ ብታዳምጠኝ፤ ቆይ እንጂ ትርሲት ጋር ደውዬ እደውልልሃለሁ ብላ የሱን ዘግታ ወደቤቷ በመደወል፤

"ሃሎ! መክብብ ! ትርሲትን አቅርባትና አንተ እግቢ ውስጥ ሥራህን ሥራ!"

"እሺ እትዬ"

"ሃሎ ትርሲት፥ እኔ እምልሽ! ስመክብብ ገብረብሩክ ልጁ እንደሆንሽ አድርጎ መታወቂያና ፓስፖርት እንዳወጣልሽ ነግሬሽዋል እንዴ?

"እንዲያውም እትዬ! ስነገሩ! ለመክብብ ብነግረውም እስካሁን ምንም ሚስጥር ሲያባክንብኝ አላገኘሁትም::

ለርስዎ እንኳ መነገር ያለበትን የእኔን ሚስጥር አልነግረዎትም::"

"እኔም አስቤው ነበር:: መክብብ ማለት በሚስጥር አጠባበቅ በደንብ የሰለጠነ" አለች ለራሷ ወ/ሮ አረጋሽ:: "ግንኙነታችሁንማ የወንድምነት ሳይሆን የፍቅር እንደሆነ እኔም ገብረብሩክ ደርሰንበታል:: እናንተ ግን ስለራቃችሁን ደበቃችሁን::"

"ኧረ በስመአብ፣ እትዬ በጣም የማይመስል ነገር ነው:: እኛ እርስዎ ስለሚያሳዝኑንና ስለምንወድዎ ለምን እንደብቅዎታለን?"

"ሆሆይ፣ የዘመኑ ልጆች ታላላቆቻቸው ምንም የሚያውቁ አይመስላቸውም ይባላል:: ከነስሙ 'የድሮ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንኳን አገራቸውን ዓለምን መምራት ይችሉ ነበር ሲባል አልሰማሽም? የምትያቸውን አገናዝቦ ለመቀበል የሚሳነኝ አይደለሁም:: እንዳልሽው ብትወዱኝማ ኖሮ ሚስጥራችሁን አትደብቁኝም ነበር:: ለማንኛውም እንድታውቂው የምፈልገው መታወቂያሽና ፓስፖርትሽ ሊቀየር የቻለው ጉዳዩ እበሳይ እካል ድረስ ስለደረሰ ገብረብሩክ ራሱን ነጻ ለማድረግ ሲል ነው:: አንቺም ብትሆኚ ራስሽን መጠበቅ ይኖርብሻል:: በምን ሁኔታ እኛ ጋ እንዳለሽ ካወቁ ባንች ላይ ብቻ ሳይሆን በእኛም ላይ ችግር ይፈጥራሉ:: በይ ለቡና ሳርፍ ነው::"

ገብረብሩክ ከመክብብና ከትርሲት ክቤቱ ማንን በዘዴ ማባረር እንዳለበት ሲያወጣና ሲያወርድ ለረጅም ጊዜ እንቅልፉን አጥቶ ነው የከረመው:: ሁለቱንም ቢያባርራቻቸው



በአንድ ላይ ሆነው ነገር ሊያመጡበት ይችላሉ:: በአንድ በኩል ይጥቀመው እንጅ [redacted]ሳ በኩል ገብሬይ በደንብ አድርጎ አስር ቁጥር ምስማር አስገብቶለታል:: ትርሲትን ክቤት ማባረሪያ ጥሩ አጋጣሚ ተፈጥሮለታል:: ጠላት እንዳይበዛበት መክብብን የማስቀሪያ ዘዴ እየፈጠረ ለወ/ሮ አረጋሽም ስለ መክብብ ጥሩ ጥሩ ነገር እያወራላት ራሱን ከፉኛ ትዝብት ላይ ጥሏል:: ትርሲትን ማስደነጋገጡን ግን ቀጥሏል:: እልፎ እልፎ "ትስሚኛለሽ፣ የጀርመኑ ነገርሽ አክትሞለታል:: ሌላ አገር ሂደሽ ከዚያ ወደ ጀርመን ሞክሪ" እያለ እቅድ አውጭ ሆኗል:: ሌላም ሌላም ማስደንገጫ ተንኮል እያውጠነጠነላት ነው::

በልባ "ድርስ አንተ ጭራቅ ቤት ስርመጠመጥ ልኖርልህ ነው ?" ትላለች:: ለነገሩ እህቷ የተፈጠረውን ችግር በዝርዝር ስለምታውቅ፣ በበኩሏ ብዙ መንገድ እያመቻቸች ነው:: ያልሞከረችው የቪዛ ደላላ የለም::

ወ/ሮ አረጋሽ እንዳንዴ ቀበጥ ወይም ሰነፍ ያደርጋታል:: ላለመጣራት ደውል ማንቃጨል ይቀናታል:: መክብብ ብቻዋን እንዳለች ያውቅ ስለነበረ "እመት እትዬ" ብሎ ሮጦ ገባ::

"ስማ መኩ፣ ያለፈውን ትተን እንደ በፊታችን እንሁን:: የሚገርምህ የገብረብሩክ ወላዋይ መሆን በጣም ገርሞኛል:: አየህ እኔና ገብረብሩክ ከመጋባታችን በፊት በተለይ እሱ ምንም ሳይኖረው ለትዳር የበቃነው ትህትናው ቀልዶቹና ቁም ነገሮቹ ማርከውኝ አፍቅሬው ነው ያገባሁት:: ገብረብሩክን እንዳፈቅረው ያስደረጉኝን ከግዜ ወደ ግዜ

እያጠኗቸውና እየተመናመኑ ናቸው። አደራህን ዝርዝሩን እንዳትጠይቀኝ። ብዙ ውሸትም እያገኘሁበት ነው። እኔ የህግ ባለቤቴን ምን እመራመረኝ እያልኩ ያወራልኝን ሁሉ እሺ ብዬ ለቀበለው አረጋሽ ሞኝ እያለ በየፖለቲካ ስብሰባቸው ላይ ለጓደኞቹ የሚያማኝ እየመሰለኝ መጥቷል።"

መክብብ 'ያበጠው ይፈንዳ ብሎ' "ውውይ... ጋሼ ! በጣም ስህተተኛ ሰው ናቸው። እውነቱን ልንገርዎትና፣ የእርስዎ ነገር ባይሆንብኝ ኖሮ ከጋሼ ጋር አንድ ቀንም አላድር ነበር።"

"ሰውን ብዙ ስታውቀው ወይ ትወደዋለህ ወይ ትጠላዋለህ" እንደሚባለው ነው። እየሀ መክብብ፣ ከሰው ጋር ሲኖር ተቻችሎ፣ አይቶ እንዳላዩ እየሆኑ ካልሆነ ችግር ነው ከሰው ጋር መኖር።" ቆይ እንዴ ብላ በእጇ ላይ የያዘቻውን ወረቀት እያነበበች እንገቷን ትነቀንቃለች። አንብባ ስትጨርስ "ድንቄም ደህንነት!" ተሳለቀችበት። የነገብረብሩክ የሰሞኑ የፖለቲካ ፕሮግራማቸው ነበር። "ይቅርታ መክብብ፣ ገብረብሩክ ሳይመጣብኝ እንብቤ ልመልስ ብዬ ነው።"

"እንዴ ከእርስዎ የሚደበቅ ሚስጥርም አላቸው እንዴ? ሲላት፤

"በሚገባ" አለችው። "የደህንነት ሠራተኛ መሆኑን አትዘንጋ። የሚገርምህ ዝርክርክ፣ ብር በጣም የሚወድ ትንሽ ስግብግብ ያለ ሰው ነው። በመሠረቱ የደህንነት ሥራ ከባድ እንደሆነ ሲሉ ሰምተህ ወይም እንብበህ ከሆነ ለሲአይኤ፣ ለሞሳድ፣ ለኬጂቢ ይሠሩ የነበሩ ሰዎች የጻፏቸውን ካነበብክ የምትገነዘበው ነገር ቢኖር የማይሆኑት ነገር የለም። የእርጻታ



ማስተባበሪያ ሠራተኛ፣ እስመጭና ላኪ፣ ... ብቻ ይገለባበጣሉ። ገብረብሩክ በእነሱ ህይን የመዋዕለ ህጻናትና የኮሌጅ ምሩቅ ያክል ነው ልዩነቱ። አታይም በዚች ልጅ የገባው ችግር። ለእሷ እዝኖ መሰለህ። የቤተሰቦቿን ንብረት በስሙ አዙሮ ለመብላት ሲሯሯጥ አይደለም በገዛ ጓደኞቹ ተጋልጦ በከባድ ምርመራ ላይ ያለው። ሰላስ የተባለችው የኢሚግሬሽን ሠራተኛም ከገብረብሩክ ጋር በመመሳጠሯ ከሥራዋ ታግዳለች እሉ። መዘዙ ሌላም ቤት እያንኳኳ ነው። ለዚህ እንኳ ትንሽ እላዝንለትም። እራሱ እንደገባበት ይወጣው። ትርሲትን ግን እኔ ባለ እቅሜ እግዟታለሁ" ስትል፣ ቀበል እድርጎ "የትርሲትማ ነገር እንጀት ነው የምትበላው። ይቺን የመሰለች ብሩህ እእምሮ ያላት ልጅ በህክምና፣ በምህንድስና ወይም ባስፈለገው መስክ ተሰማርታ ተምራ ተመራምራ ብዙ ቁም ነገር ልትሰራ የምትችል ልጅ ችግሮች እየተደራረቡባት ነጋ ጠባ መፍትሄ ፍለጋ ታሰላስላለች። ከኔ ጋር እንኳን ንግግር ካቆምን ስንት ቀናችን። ዝም ብላ ታለቅስዋለች። የሷ ጭንቀት የኔ ጭንቀት፣ ለቅሶዋ ለቅሶዬ እየሆነ እኔም በጭንቀት ላይ ነኝ።"

"ወይ መክብብ፣ እኔንም እግዜር ይቅር ይበለኝ። የዚህን ሰውዬ ወሬ ለቅሚ ለቃቅሚ ችላ ብያታለሁ። ትጨነቃለች፣ ነገር ታወጣለች፣ ታወርዳለች ሳልከው፣ ግድ የለም። እቅጣጫውን እይሳት እንጂ መጨነቅ፣ ማውጣትና መውረድ ለብዙዎቻችን ጉዳቱ ብቻ ነው እንጂ የሚታየን ጥቅምም እለው። ህይወታቸው አለውጣ ውረድ ቀጥ ብሎ የተቃናላቸው እንድ ቀን ችግር ቢገጥማቸው የሚይዙት የሚጨብጡት ነው የሚጠፋቸው። እንዳንዶቹ ቀበጦችማ ምግብ እንኳ ተዘጋጅቶ

ካልጠበቃቸው ምግብ ካለበት ቦታ አንጎዳጉደው ላለመፈለግ ደንግጠው ይወጣሉ ወይም ተጠቅልለው ይተኛሉ። አይብዛ አይደጋገም እንጂ መቸገር ጥሩ ነው። ትልቁ ነገር በምንም አይነት ተስፋ አለመቁረጥ ነው። የማያልፍ ነገር ደግሞ የለም። ዳገት ካለ ቁልቁለት እንዳለ ሁሉ ስለ ትርሲትም ጊዜያዊ ችግር ደስታ ይኖራል። ዋናው መታገስ ነው። ወይ አንተ ልጅ አስለፈለፍከኝ! እንዲህ ወሬዬን ስስልቅ ገብረብሩክ ምን ይለኝ እቴ" እንዳለች።"

"እንዲያው የታዘቡኝን ታዘቡኝ እንጅ የጋሼን ወሬ አይሰሙ። ጋሼ ይዋሻሉ። እኔ በደምብ መረጃ አለኝ። ተንኮልም አላቸው።"

"እይ ከእንግዲህ የምታለል አይመስለኝም። በል አረፍ ልበል። "

ቀኖች ይመሻሉ፤ ሌቶች ይነጋሉ ጊዜው ይሮጣል፤ "ስማ መክብብ፣ ናስቲ እንዴ" አለው ገብረብሩክ መክብብን አንድ ቀን በጥዋቱ። "ማንም ሰው መጥቶ ትርሲትን ቢጠይቅህ የለችም ማለት አለብህ።"

"እሺ ጋሼ ደህና ዋሉ።" ብሎት እንደወጣ ትርሲት ተደብቃ ከምታይበት ብቅ ብላ "መክብቤ ለዚህ ጭራቅ እጅ ትሰጣለህ፣ 'አስረግዞኛል እኮ'" ብላ ልክ መርዶ እንደተረዳ ለቅሶዋን በጩኸት አነባችው። " እቤት ጉድ ጉድ" እያለ መክብብም አላቀሳት እና፤ እንደምንም ራሱን ተቆጣጥሮ እሷን ማባበል ያዘ። የባዮሎጂ አስተማሪው ስለ ዘር ሲታስተምር በወሬ ወሬ ተነስቶ ሦስት ወር ካላለፈው ያልተፈለገ ጽንስን ማስወረድ ይቻላል ያለችው ትዝ ብሎት "ትርሲትዬ፣ አይዞሽ



ከደፋው ሚካኤል" ጋር መፍትሄ እናጣም" ሲላት፣ "መክብቤ ከጉድ አውጣኝ" እያለች እላዩ ላይ ተጠመጠመች፣ "አይዞሽ የእኔ እህት፣ በይ ነይ ፊትሽን ታጠቢና ቁርሳችንን እንብላ። ብሎ ሃሳቧን ለማስቀየርሞከረ።

ስልክ እየጮኸ ነው። "መክብቤ ጭራቁ ከሆነ የለችም እቤት በለው።"

ገብረብሩክ ነበር። ለነገሩ ራሱን ነው የፈለገው።

"ስማ መክብብ፣ ከቦሌ ፒያሳ የሚለውን ታክሲ ያዝና ቶሎ ና። ሲኒማ ኢትዮጵያ ጋ እጠብቅሃለሁ" ሲለው" እሺ " ብሎ ስልኩ ተዘጋ።

"ይኼ ጭራቅ ይህን ጊዜ እዚህ አካባቢ ሆኖ ደውሎ ይሆናል። አንተ ስትወጣለት እኔን ለማነቅ፣ ዝም ብለህ ቆይ እባክህ መክብቤ፤ እቤት እንኳን ቢያገኝህ ሳንቲም ረስቼ ተመልሼ ነው ትለዋለህ" ተባብለው ቁርሳቸውን በላልተው ብዙም ሳይቆዩ በር በዘነዘና የተደበደበ ያክል በር ለጉድ ጮኸ።

"እቤት! ጋሼ ሳንቲም ረስቼ ተመልሼ ልክ ልወጣ ስል ነው የመጡት" እያለ ተርበድብዶ በር ሲከፍት ያልታሰቡ ሦስት ነጭ ለባሾች ሽጉጣቸውን እያብለጨለጩ "ትርሲትን ጥራት" ሲሉት "እረ የለችም" ብሎ ሲሟገት በሽጉጡ ሰደፍ ግንባሩን ሲመታው መክብብ ወደሁዋላው ተዘረረ። ትርሲት ገብረብሩክ ከሆነ ከመክብብ ጋር ባዘጋጀች ማምለጫ ለማምለጥ ቀስ ብላ እያሾለከች ነበር። ሁኔታውን ስታይ በጣም ተደናግጣ "ዋይ! ዋይ! ወይኔ ወንድሜ እያለች ልታነሳው ስትሮጥ ሁለቱ ግራናቀኝ እጇን ያዟት። "ፀጥ በይ አንቺ" ብሎ አንደኛው በጥፊ ፊቷን ፍም እስመሰለው። "እንቺን ፍለጋ ነው

የመጣነው። "በይ [redacted] መታወቂያሽንና ፓስፖርትሽን ያዥ፣ ካባትሽ ሂጅና ተደባለቂ።" ብለው እቃዋን አሽከመው የግል መኪና በመሰለች ቶዮታ ዲኤክስ አፍነው ወዳልታወቀ ቦታ ይዘዋት ነጎዱ።

ደሙን እየጠራረገ "ወይኔ መክብብ! ግድ የለም 'ለሁሉም ጊዜ አለው' በደንብ ባላያቸው ይቆጨኝ ነበር፣ እንኳን ከፍያ በጭምብልም ፊቱን ቢሸፍን አይጠፋኝም። ትርሲት ጥሩ ስም ስጥታዋለች። የጭራቁ ጓደኞች ናቸው። ጓደኞቹን ልኮ ልጅቷን አሳፈናት። ኧረ ምን ጉዱ ወንጀለኛ ነው። ለማየትም፣ ለመስማትም የሚሰቀጥጥ የሠይጣን ሥራ" እያለ አውጥቶ አውርዶ ሃሳቡን ተወት አደረገና ተጣጥፎ ቁጭ ብሎ ደብዳቤ መጻፍ ያዘ።

ገብረብሩክ የሠራውን ሥራ ስለሚያውቅ በሥራ እንደተወጠረ ለወ/ሮ አረጋሽም ስለነገራት በጊዜ እንደማይመጣ ታውቋል። መክብብም መጥቼ አጣሁህ ለማለት ተዘጋጅቶ ነበር። ሊያባርረው እንደሚያስብ በደምብ ገብቶታል። እሱንና ትርሲትን ያስጨነቃቸው ግን ለወ/ሮ አረጋሽ እንዴት እንደሚነግሯትና ከዚያ በሁዋላስ የት እንደሚኖሩ፣ የትርሲት የገቢ ሁኔታ እንዳይደናቀፍ ነው የሚያወጣው የሚያወርደው።

"ቆይ ከዚያ በፊት" ብሎ አባቱ ጓደኞች ጋ ሲደውል "በቃ ዛሬ ወይም ነገ የመጨረሻ ቀንህ ነው ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶልሃል" ተብሎ ጥሎ ለመሄድም ቆርጧል። በታዘዘው መሠረት የቀልፍ ማባዛቱን ነገር ሁሉ ጨርሷል። የመኪናዎቹ ሳይቀር።



"ይህንን ደብዳቤ የጻፍኩልዎ የመጫወቻ ጊዜ ከሌለን ብዬ ነው። ለሩህሩሁዋና ለደጓ እትዬ! እንኳን የሚከባበር፣ እንኳን የሚተሳሰብና የሚዋደድ ታላቁ የሰው ፍጡር ቀርቶ እንስሶችም ባይለያዩ ነው የኔ ምኞት። እትዬ! ባለፈው ጊዜ በተለይ ያባቴን ነገር ሳጫውትዎ እንባዎትን ለአባቴ ማዘራትዎ ሳያንስዎ እይዞህ አለሁልህ! ያሉኝ የዘወትር የመንፈስ ምግቤ ሆኗል። የሆነ ሆኖ በርስዎ በኩል ምንም ያደረጉኝ ነገር ባይኖርም በትርሲት ላይ የተደረገው ሴራ ተቆርቋሪ ሰው ጋሼን መጠየቅ ባይችል እግዜር ይጠይቃቸዋል። እኔ የምፈራው ለሃጥአን የወረደው ለጻድቃንም እንዳይተርፍ ነውና እርስዎን አምላክ ይጠብቅዎት። መዘዛቸው ለእርስዎት እንዳይደርስ ይጠንቀቁ። ፍንጭ ለመስጠት ያክል፣ ያ የጋሼ ጓደኛ ሁልጊዜ እሁድ እሁድ እየመጣ እለ ሀረር ቢራ አልጠጣም የሚለው ነው እኔን የፈነከተኝና ትርሲትን በጥፊ የመታት። ጋሼማ ትርሲት ለትወሰድ እኔ እንዳላይ ዘዴ ቢጤ ፈጥረው ወደ ፒያሳ ጠርተውኝ ነበር። ሳይሳካላቸው ቀረ እንጂ። ለማንኛውም ትልቅ ሚስጥር ስለሆነ ይህን ደብዳቤ እንብበው ያቃጥሉት።

እናም ነገም የኔ እጣ እንዲሁ ሊሆን ስለሚችል የምሄድበትንም ባላውቅም ለጊዜው ከናንተ ቤት ዞር ልል ወስኛለሁ። የጋሼ መዝዝ ስል ትርሲትዬ ስቃይ የሚደርስባት ጋሼ ባደረሱባት አጸያፊ ተግባር፣ በተለይ በእኛ ኢትዮጵያኖች የተወገዘ ርህራሄ የጎደለው አረመኔያዊ ድርጊታቸውን ለመሸፋፈን ነው። የሳቸውን ነገር ግን እግዚአብሄር ይፍረደው። እትዬ፣ እውነቱን ለመናገር የእርስዎ ባለቤት ስለሆኑ ጋሼ፣ ጋሼ አንቱ፣ አንቱ እያልኩ ጻፍኩ እንጂ በዓለም ላይ ክብር የሌላቸው

መሪዎች፣ ወንጀለኞች፣ አስገድዶ ደፋሪዎች፣ በአጠቃላይ ለነዚህ መጥፎዎች የተሰጠው ስም መጥፎዎች ቢሆን ኖሮ መጥፎው ገብረብሩክ እያልኩ ብጽፍልዎት ደስ ይለኝ ነበር:: ግን የእርስዎን ክብር መንካት እንዳይሆን ብዬ ትቸዋለሁ:: ባመቸኝ ጊዜ እየደወልኩ ሰላም እልዎታለሁ::" ብሎ እየጻፈ ገና ሃሳቡን ሳይቋጭ በሃሳብ ጭንቅላቱ ተወጠረ:: በጥያቄ እራሱን ማፋጠጥ ያዘ:: ጣቱን አየቆጠረ

፩ኛ. ትርሲትን ከዚህ ቤት ከወጣሁ እንዴት አገኛታለሁ

፪ኛ. እርግዝናዋን እንዴት ነው ለአትዬ ፍርጥርጥ አድርጌ የምነግራቸው፣ ትርሲትዬም እድሉ ካጋጠማት የማይኖሩበትን ሰዓት ለለምታውቅ ስልክ ልትደውልልኝ ስለምትችል ዋጥ አድርጌ በትእግስት ልቆይ" ብሎ ሊያስብ ቆየና የጻፈውን ወረቀት በጫጭቆ ሽንት ቤት ውስጥ ጨመረው::

መክብብ ፊቱን እያሻሸ በሃሳብ ተውጦ እያለ ስልክ አንቃጨለ:: ማንም ይሁን ማን ግድ ሳይለጠው አንስቶ በማቃሰት ድምጽ "ሃሎ" ሲል፣ ደዋዩ የመክብብን ድምጽ በመጠራጠሩ መክብብ መሆኑን አረጋገጠና "ታዲያ ምነው ድምጽህ ተቀየረ" ሲለው የተፈጠረውንና የደረሰበትን ያስታወሰውን ያህል ካስረዳው በሁዋላ አድርግ የተባለውን ለማድረግ ጥድፍ ጥድፍ ማለት ያዘ::

በተፈጠረው አጋጣሚ የመክብብ ጉዞ ገብረብሩክንም አጉል ማስጠንቀቅ ይሆናል ብለው ለለሰኑ ለተወሰነ ጊዜ ተራዝሟል::



"ሃሎ ጋሼ መክብብ ነኝ" ሲል ገብረብሩክ ምንም እንደማያውቅ፣ "ሃይ መኬ እንዴት ነህ" ሲለው አሞካሽቶት ሳያውቅ ዛሬ ሲያሞካሸው በጣም እየገረመው "ጋሼ እቤት ውስጥ ችግር ስለገጠመን ልነግረዎት ብዬ ነው"

ገብረብሩክ በመጣደፍ "ምን አይነት ችግር?"

"ትርሲትን ወሰዷት፣ እኔንም ደብድበውኝ ገና መንቃቱ ነው" ብሎ ሳይጨርስ "ሰዎቹን ታውቃቸዋለህ? ምን ይመስላሉ?" እያለ በጥያቄ አጣደፈው:: መክብብ ጥያቄው በጣም ስለገባው፣ ምንም አይነት ግንዛቤ እንደሌለው ነግሮት በደስታ እፎይ አስባለው:: "በቃ እንገዲህ ጋሼ! እስኪመጡ ሃኪም ቤት ደርሼ እመለሳለሁ::"

"ለአረጋሽስ ነገርካት?"

"እይ ለእርስዎ ከነገርኩዎት ይበቃል ብዬ ነው::" ለሱ የተሻለ አቅርቦት ያለው ለመምሰል እየጣረ::

"ጥሩ በል አይዞህ ማታ አይሃለሁ:: " ብሎ ስልኩን ዘግቶ ወዲያውኑ ወደ አረጋሽ ደውሎ፣

"ሃሎ አረግዬ ዛሬ ጉድ ሆነናል፣ አላት:: "ምን? ምን ተፈጠረ?" እያለች በጥያቄ ስታጣድፈው "ትርሲትንም ወሰዷት፣ መክብብም አጉል ተናንቆ እድናታለሁ ሲል ግንባሩን ተርትረውለት አሞኛል ወደሃኪም ቤት መሄዴ ነው ብሎ ደውሎልኝ ነበር:: ቤቱ ባዶ እንዳይሆን ከቻልሽ ወደቤት ብትሄጂ ጥሩ ነው::"

"ወ/ሮ አረጋሽ ስልኩን ዘግታ መክብብ እንዴት እኔ ጋ ሳይደውል ወደሱ ጋ ደወለ፣ ገብረብሩክስ ቢሆን በማዘን ፋንታ

እንዴት ግንባሩን ተረተሩለት ይላል? ብዙም ጊዜ ሳታባክን ወደቤት ስልክ እንዳቃጨለች ስልኩ ደግሞ ደጋግሞ ጠራ፡ መልስ የለም፣ ረጭ ሆነ።

እነ ዶክተር ፋሲል በአስቸኳይ ለመክብብ መኪና ልከውለት ሆስፒታል ደርሶ አስፈላጊውን እርዳታና ምክር ተደርጎለት በሆስፒታል ውስጥ እንዲቆይ ተወሰነ።

ወ/ሮ አረጋሽ እቤት እንደደረሰች ባለቤቷ ጋ ደውላ "ስማኝ ገብረብሩክ፣ ቶሎ ናና ጊዜ ሳናጠፋ በቤታችን ውስጥ የተፈጠረውን ሁኔታ ለፖሊስ ማስታወቅ አለብን። ብላ ገና ሳትጨርስ፡ "አንቺ ደግሞ ህጻን አደረግሽኝ፣ እስካሁን ምን ሥራ የቆየሁ መሰለሽ?"

"በጣም ጥሩ አብረን እንሂድና፣ ማለቴ መክብብም ይዘን ስለተፈጠረው ሁኔታ ብናስረዳ መልካም ይሆናል ብዬ አስባለሁ።"

"ምን እንደሆነ ሳታውቂ ምን ብለሽ ልታስረጂ ነው? ወይስ መክብብ የነገረሽ ነገር አለ?

"አንተ ደሞ ትቀልዳለህ። 'አፈር በሆንኩት' እኔስ እንዴት ጉዳት እንደደረሰባቸው እንኳ ገና ሳልጠይቀው ምን ለወሬ አስሮጠኝ ብለህ ነው? ለማንኛውም ስልክ ብደውልም አላነሳው ስላለኝ ሃኪም ቤት ይሆናል፡ በል እቤት ቶሎ ና ቻው።"

"እቤት እንኳ ባሬ በጊዜ አልመጣም። ይህንን ጣጣችንን መልክ መልክ ለማስያዝ ብዙ መውጣት መውረድ አለብኝ።

"ጣጣ አልከው?"



"የኔን ስቃይ ልበልሽ?"

"እንደተመቸህ፣ በል ደህና እምሽ።"

እቤት ውስጥ እንደገባች "መክብብ ኧረ መክብብ! እንደው እንዴት ሆነህ ይሆን? አፏን በጣቶቿ ሸፍና በሃሳብ ተውጣ ቆይታ ወደ ዶ/ር እስክስታ ጋ ስልክ ደወላ፣

"ሃሎ! መንጌ"

"መንገሻ አይደለሁም"

"በል ቀልዱን ተው፣ ታዲያ መንገሻን ትቼ ዶ/ር እስክስታ ልበልህ?"

"ግድ የለም ላንቺ ይፈቀዳል!"

ዶ/ር መንገሻ ትክክለኛ ስሙ ሲሆን፣ እስክስታ የሚል ቅጽል ስሙን ያገኘው ከእስር ቤት ከወጣ በኋላ ሲሆን በዚያ በኢሕአፓ ስበብ እግሩን መትረው መትረው ሲበቃቸው ከወረወሩት በሁዋላ አገግሞ ትምህርቱን ጀምሮ ገና የመጀመሪያ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሳለ ሲራመድ ህመሙ ስለሚሰማው፣ መርገጥ ስለሚሳነው ቶሎ ቶሎ ብድግ ብድግ ስለሚያደርገውና ሰውነቱ ስለሚንቀጠቀጥ "እስክስታ" የሚወርድ አስመስሎበት "እስክስታ" የቅጽል ስሙ ሆኖ ነው የቀረው። ወ/ሮ አረጋሽም ታሪኩን አብጠርጥራ ስለምታውቅ "እስክስታ" ስትለው ብዙም አይከፋውም።

"በይ እንግዲህ አንቺ በየክሊኒኩ ደዋውይ እኔ በየሆስፒታሉ ልሞክር"።

"ከብዙ መከራ በኋላ ዶ/ር መንገሻ መክብብ ያለበትን ሆስፒታል አግኝቶ ለወ/ሮ አረጋሽ ካስረዳት በኋላ ደግሞ እንደሚደውልላት ተነጋግረው ተሰነባበቱ።